መልእክት ሰባት

**ነህምያ—ለእግዚአብሔር**
**ዘመን ቀያሪ ዋጋ ያለው ሰው ምሳሌ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ራእ. 12፥1-14፤ ነህ. 1፥1-11፤ 2፥9-20፤
4፥4-5፣ 9፤ 5፥10፣ 14-19፤ 8፥1-10፤ 13፥14፣ 29-31

I. **የእግዚአብሔር መሻት ይህንን ዘመን መዝጋት እና የመንግሥቱን ዘመን ማምጣት ነው፤ እግዚአብሔር ይህንን ይፈጽም ዘንድ ዘመን ቀያሪ መሣሪያ ሊኖረው ይገባል:-**

ሀ. ለእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ ዋጋ ያለን እንሆን ዘንድ ሁላችንም ወደ ጌታ መመልከትና መጸለይ አለብን፤ ይህንን መግቦተ ዘመን ለመዝጋትና ቀጣዩን ዘመን፣ የመንግሥቱን ዘመን ለማምጣት ምን እያደረግን እንዳለን ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፤ ይህ ልዩ ጊዜ ነው፣ ስለዚህ ልዩ ሥራን ለመሥራት ልዩ የሆኑ አማኞች አስፈላጊነት አለ።

ለ. “ኑ” ሳይሆን “ሂዱ” ብቻ ማለት የሚችሉ ምንም ውጤት አይኖራቸውም፤ ማለትም ለእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ ዋጋ አይኖራቸውም—ተዛ. ዕብ. 10፥22:-

1. የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ለአማኞች የነገራቸው ወደ ፊት እንዲሄዱ ሳይሆን ወደ ፊት እንዲመጡ ነው፤ ይህም ማለት ጸሐፊው አንድ ልዩ በሆነ ቦታ እንደነበረና አንባቢዎቹ እርሱ ወደነበረበት ስፍራ እንዲመጡ ፈልጓል ማለት ነው።
2. ወደ ሦስት ነገሮች ወደ ፊት መምጣት አለብን፡ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን፣ ወደ ጸጋው ዙፋን እና ወደ እግዚአብሔር ወደ ራሱ፤ ወደ ኋላ አታፈግፍጉ—ወደፊት ኑ—ቁ. 22፤ 4፥16፤ 7፥25፤ 11፥6።
3. እግዚአብሔር በጸጋው ዙፋን ላይ ነው፣ የጸጋው ዙፋን ደግሞ ያለው ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነው፤ የዕብራውያን መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ፣ ጸሐፊው አማኞች ወደ ፊት እንዲመጡ እየጠራ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነበር።

ሐ. የወንዱ ልጅ ወደ ሰማይ መነጠቅ፣ የሰይጣን ወደ ምድር መጣል እና መንግሥቱ ስለ መምጣቱ በሰማይ ያለው አዋጅ፣ እግዚአብሔር ወንዱን ልጅ ማግኘቱ ታላቅ የሆነ ዘመን ቀያሪ እንቅስቃሴው እንደሆነ ያመለክታል፣ ምክንያቱም ይህ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ያጠናቅቃል፣ የመንግሥቱን ዘመንም ያመጣል—ራእ. 12፥5፣ 9-10፤ 11፥15።

መ. የወንዱ ልጅ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መነጠቅ ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን፣ ይህም ከሦስት ዓመት ተኩሉ (አርባ ሁለት ወራት) የታላቁ መከራ ጊዜ በፊት ይሆናል—12፥1-14፤ 13፥5፤ 11፥2።

ሠ. የምንኖረው ለእግዚአብሔር ብዙ ልናደርግ በምንችልበት፣ እጅግ ልዩ የሆነ እድል ባለበት ጊዜ ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ብርሃን መንገዱን ያሳየናል፣ በውስጣችን የሚኖረው ክርስቶስ ግን እንደ ብርታትና ኃይላችን መንገዱን እንድንጓዝ ያስችለናል፤ አሁን ጥቅም ላይ እንውል ዘንድ ታላቅ ዋጋ መከፈል አለበት—3፥18።

II. **ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓላማ ጋር ስላልደረሰች፣ እግዚአብሔር ዓላማው ጋር የሚደርሱና መጠይቁን የሚያሟሉ የድል ነሺዎች ቡድን ይመርጣል፤ ይህ የወንዱ ልጅ መርህ ነው—12፥1-2፣ 5፣ 10-11፤ 2፥7፣ 11፣ 17፣ 26-28፤ 3፥5፣ 12፣ 20-21:-**

ሀ. አጽናፍ ዓለማዊቷ ብሩህ ሴት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጥቅል-ድምር ትወክላለች፣ በመጨረሻም በዘፍጥረት 3፥15 ላይ ያለው የሴቲቱ ዘር በወንዱ ልጅ የተመሰለውን ድል ነሺ አማኞችን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠንካራውን ክፍል ለማካተት ተልቋል—ራእ. 12፥1-2፣ 5፣ 10-11።

ለ. የቀደመው እባብ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመፈጸም እና ይህን ዘመን ለመቀየርና የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጥ ለማምጣት የእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ መሣሪያ ለመሆን፣ የእባቡን ራስ በውስጣችን ለመቀጥቀጥና እኛን ብዙዎች የተካተቱበት የሴቲቱ ዘር፣ ድል ነሺው ወንዱ ልጅ ለማድረግ፣ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ ወደ ውስጣችን የታደለው የተለወጠው የሴቲቱ ልጅ፣ የሴቲቱ ዘር ነው—ቁ. 5።

ሐ. መዝሙር 2፥8-9፣ ራእይ 2፥26-27 እና ራእይ 12፥5 ጌታ ኢየሱስ በእግዚአብሔር እንደ ተቀባው፣ በአብያተ ክርስቲያናት ያሉት ድል ነሺዎች እና ወንዱ ልጅ አሕዛብን በብረት በትር እንደሚገዙ ያመለክታሉ፣ ይህም ጌታ ኢየሱስ፣ ድል ነሺዎቹና ወንዱ ልጅ አንድ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ጌታ እንደ መሪው ድል ነሺ (3፥21) የወንዱ ልጅ ራስ፣ ማዕከል፣ እውነታ፣ ሕይወትና ባሕርይ ነው፣ ወንዱ ልጅ ደግሞ እንደ ተከታዮቹ ድል ነሺዎች የጌታ አካል ነው።

መ. በጌታ የመስቀል ላይ ሞት ሰይጣን፣ የቀደመው እባብ ተፈርዶበታል፣ ወደ ውጭ ተጥሏል (ዮሐ. 12፥31፤ 16፥11)፤ ያ ፍርድ በመጨረሻ እንደ ወንዱ ልጅ፣ ብዙዎች እንደተካተቱበት የሴቲቱ ዘር በድል ነሺዎቹ ይከናወናል ይፈጸምማል፤

ድል ነሺዎቹ አማኞች በሰይጣን ላይ የሚያውጁትና የሚያካሂዱት ጦርነት በእርግጥም ሰይጣን በመጨረሻ ከሰማይ እንዲጣል በእርሱ ላይ የጌታ ፍርድ መተግበር ነው (ራእ. 12፡7-9)።

ሠ. ወንዱ ልጅ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው የሚቆሙትን፣ መላዋ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ ያለባትን ስፍራ የሚወስዱትንና የቤተ ክርስቲያንን ሥራ የሚሠሩትን ድል ነሺዎችን ያካተተ ነው—2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-28፤ 3፡5፣ 12፣ 21፤ 12፡5፣ 11፡-

1. የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በዘላለማዊ ዓላማው ውስጥ ክፍል ሊኖራቸው ይገባል፣ ነገር ግን ሁሉም ተገቢ ኃላፊነታቸውን አይወስዱም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከመካከላቸው አንድ ቡድን—በሴቲቱ የተወለደውን ወንዱን ልጅ ይመርጣል።
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ጠንካራዎቹ ለእግዚአብሔር ውጊያን የሚዋጉ እና የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር የሚያመጡ አንድ የጋራ አሃድ ተደርገው ይቆጠራሉ—ራእ. 12፡5፣ 10-11።
3. እግዚአብሔር ኢኮኖሚውን ለመፈጸምና ዓላማውን ለማከናወን ወንዱን ልጅ ይጠቀማል—1 ጢሞ. 1፡4፤ 2 ጢሞ. 1፡9፤ ኤፌ. 1፡9፣ 11፤ 3፡11።
4. ዘላለማዊ ዓላማው ይፈጸም ዘንድ እግዚአብሔር ጠላቱን እንዲያሸንፍና መንግሥቱን እንዲያመጣ ወንዱ ልጅ ያስፈልገዋል፤ የጌታ ምለሳ ዛሬ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ተግባራዊነት ነው፣ ኢኮኖሚው ሊከናወን የሚችለውም በወንዱ ልጅ ብቻ ነው—ራእ. 12፡10።

ረ. የወንዱ ልጅ መነጠቅ ከዚያ ወዲያ ሰይጣን በሰማይ ምንም ሥፍራ እንዳይኖረው የሚያደርግ ልውውጥ ነው፤ ፍርዱን ጠላቱ ላይ በመተግበር የእግዚአብሔርን ፍላጎት ለመፈጸም መነጠቅ አለብን—ቁ. 5፣ 7-10።

ሰ. ወንዱን ልጅ የሚያዋቅሩት ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ፣ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ ስለማይወዱ ዲያቢሎስን (ከሳሹን፣ ተሳዳቢውን) እርሱም ሰይጣንን፣ የእግዚአብሔርን ጠላት ድል ይነሡታል—ቁ. 10-11።

ሸ. ክርስቶስ ራሱን ወደ ልባቸው ውስጥ እንዲሠራ በየዕለቱ ወደ ውስጡ ሰዋቸው ስለሚጠነክሩ፣ ፍሊጋ የሌለውን የክርስቶስን ብልጥግናዎች እየተመገቡ ስለሆነ እና ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ስለሚለብሱ የወንዱ ልጅ መላው ማንነት በክርስቶስ ንጥረ-ነገር የተሞላ እና የተሰረገ ነው—ኤፌ. 3፡16-18፣ 8፤ 6፡10-11።

**III. እስራኤል ለሰባ ዓመታት በምርኮ በተወሰደ ጊዜ፣ እውነተኛ ድል ነሺ ከነበረው ከነህምያ የተነሣ እግዚአብሔር ያኔም ዘመን ቀያሪ እንቅስቃሴ ነበረው፤ እርሱ ለእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ ዋጋ ያለው ሰው ምሳሌ ነው—ነህ. 1፡1-11፤ 2፡9-20፤ 4፡4-5፣ 9፤ 5፡10፣ 14-19፤ 8፡1-10፤ 13፡14፣ 29-31፡-**

ሀ. በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ ወሳኙ ነገር የኢየሩሳሌም ከተማ ከቅጥሯ ጋር መልሶ መገንባቱ እንደ እግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ለምስክሩ በምርጦቹ መካከል ያለ ቀጣይነት ያለው ምለሳ መሆኑ እና በከተማይቱ ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር ቤት ከለላና ጥበቃ መሆኑ ነበር፡-

1. ይህ የሚያመለክተው እንደ ማደሪያው እና በምድር ላይ እንዳለ ቤቱ፣ የእግዚአብሔር ቤት፣ እርሱ ኢኮኖሚውን ያከናውን ዘንድ ለአስተዳደሩ በምድር ላይ ያለውን የእርሱን ፍላጎት ለመጠበቅ መንግሥቱ እንደ ከልል መመሥረት እንደሚያስፈልገው ነው—ተዛ. ሮሜ 14፡17።
2. የእግዚአብሔር ቤት መልሶ መገንባት የዘቀጠችውን ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር መመለሱን በምሳሌ ያሳያል፣ የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር መልሶ መሠራት እግዚአብሔር መንግሥቱን መመለሱን ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ቤት ግንባታና መንግሥቱ አብረው ይሄዳሉ—ማቴ. 16፡18-19።

ለ. ክርስቶስ እንደ ሕይወታችን እውን ሲሆንልን እና ስንደሰተው ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቤት አለችን፤ ጨምረን ሄደን ራስነቱ እውን ከሆነልን ቤቱ ከተማው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ለመሆን ይተልቃል—ኤፌ. 1፡10፣ 22-23፤ 4፡15፤ ራእ. 22፡1።

ሐ. ነህምያ ዛሬ በጌታ ምለሳ ውስጥ ተገቢ የሆነ ቁርጠኝነት ሊኖረን እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡-

1. የሞዓባውያንና የአሞናውያን መሪዎች ነህምያ ለእስራኤል ልጆች መልካም በመፈለጉ እጅግ ተቆጥተው ነበር፤ እነዚህ የሎጥ የረከሰ መቀጠል የነበሩት የእርሱ ዝርያዎች የእስራኤልን ልጆች ጠሏቸው፣ ናቋቸውም—ነህ. 2፡10፣ 19፤ ተዛ. ሕዝ. 25፡3፣ 8።
2. ከሚያፌዙት፣ ከሚንቁት እና ከሚነቅፉት ከእነዚህ ተቃዋሚዎች አንጻር፣ ነህምያ ፈሪ ሳይሆን በጣም ንጹሕና ቁርጠኛ ነበር—ነህ. 2፡17-20፤ 4፡1-23፤ ተዛ. ሐዋ. 4፡29-31፤ 1 ተሰ. 2፡2፤ 2 ጢሞ. 1፡7-8።
3. ቁርጠኞቹ ከእግዚአብሔር እርዳታን ይቀበላሉ፤ እንደ ነህምያ ሐዋሪያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር ተባበረ፣ በዚህ ትብብር ውስጥም የእግዚአብሔርን እርዳታ ተገነዘበ—ሐዋ. 26፡21-22።

4. ኢኮኖሚውን በማከናወን ውስጥ ለእግዚአብሔር ጠቃሚ ለመሆን በሰው ምልልሱ ውስጥ እንዳለ የስብዕና ሰናይ ባሕርይ የነህምያ ቁራጥነት ፍጥረታዊ ችሎታችን እና አቅማችን በክርስቶስ መስቀል ማለፍና ወደ ትንሣኤ ውስጥ፣ እንደ ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ወደ መንፈስ ውስጥ መግባት እንዳለበት ያሳያል።

መ. ነህምያ በተፈጥሮአዊ ሰዉ ሳይሆን በትንሣኤ ኖረ፤ ቆራጥ ነበር፣ ቆራጥነቱ ግን በሌሎች ባህሪያት የታጀበ ነበር፦

1. ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት እግዚአብሔርን የሚወድ እና ቅዱሱን ምድር (ክርስቶስን በማመልከት)፣ ቅዱስ መቅደሱን (ቤተ ክርስቲያንን በማመልከት) እና ቅዱሱን ከተማ (የእግዚአብሔርን መንግሥት በማመልከት) ጨምሮ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን ፍላጎት የሚወድ ነበር—1 ነገ. 8፡48፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 3፡1-5።
2. እግዚአብሔርን እንደሚወድ ሰው ነህምያ ኅብረት በማድረግ እርሱን ለመንካት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ለቅጥሩ መልሶ መሠራት ነህምያ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመ፣ በእርሱም መሠረት ጸለየ—ነህ. 1፡1-11፤ 2፡4፤ 4፡4-5፣ 9።
3. ነህምያ በእግዚአብሔር ታመነ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ፣ የእግዚአብሔር ወኪል ሆነ—5፡19፤ ተዛ. 2 ቆሮ. 5፡20።
4. ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ነህምያ ራስ ወዳድ ያልሆነ፣ የራሱን ወይም የግል ጥቅሙን የማይፈልግ ነበር፤ ሁልጊዜ ለሕዝቡና ለአገሩ ያለውን ለመሠዋት ፈቃደኛ ነበር—ነህ. 5፡10፣ 14-19።

ሠ. በንጉሥ ስፍራ እንዳለ ገዢ ነህምያ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በማከናወን፣ ለኢየሩሳሌም ቅጥር መልሶ መሠራት ንጹሕ ልብ ያለው ሰው ነበር፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አንድ መሪ ምን መሆን እንደሚገባው የሚያሳይ ምሳሌ ነበር—ተዛ. 1 ጢሞ. 3፡2-7፤ 1 ጴጥ. 5፡1-3፦

1. ከአብዛኛው የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት በተጻራሪ ነህምያ ራስ ወዳድ አልነበረም፣ የራሱን ፍላጎቶች አልፈለገም፣ በፍትወት ምኞትም አልታለለም።
2. እንደ ጦር አዛዥ ነህምያ፣ ጠላትን ለመዋጋት ዝግጁ በሆኑት መካከል ነበር፣ በሌሊትም ከሚጠብቁት መካከል ነበር፤ እነዚህን ጉዳዮች ለሌሎች አልተወም ይልቁንም እርሱ ራሱ በእነርሱ ተሳተፈ—ነህ. 4፡9-23።
3. እርሱና ወንድሞቹ እግዚአብሔርን ስለፈሩ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ለአለቃ የሚገባውን ምግብ አልበሉም—5፡14-15።
4. ያለ ምንም አይነት ክፍያ በከተማይቱ ቅጥር ላይ ለመሥራት ራሱን ሰጥቷል፤ የራሱን በመፈለግ ፈንታ ቅጥሩን ለመገንባት ዓላማ ሌሎችን መገበ—ቁ. 16-18።

ረ. ነህምያ ገዢ ቢሆንም እንኳን የራሱን ምኞት ለማሳካት ፈጽሞ የማይፈልግ ነበር፤ ይህ አገሪቱን መልሶ በመሥራት ውስጥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ቃል ዳግም መቀናበር ዕዝራ እንደሚያስፈልገው በመገንዘቡ ተመልክቷል—8፡1-10፤ ፊልጵ. 2፡3-4።

ሰ. ነህምያ በሰው ታሪክ ውስጥ ፍጹሙ መሪ፣ ምርጡ መሪ እና አንድ ሽማግሌ ምን መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ምርጡ ምሳሌ ነበር፤ ዘመኑን ለመቀየር እግዚአብሔርን የማትረፍና እግዚአብሔርን ወደ ሌሎች የማፍሰስ ምሳሌ እንድንሆን፣ ለሁላችንም በተለይ በቤተ ክርስቲያን ላሉ መሪዎች የእርሱን ምሳሌ ማስተዋል በእርግጠኝነት ጠቃሚ ነው—ነህ. 5፡19፤ 13፡14።

© 2022 Living Stream Ministry